

# የኢየሱስ ክርስቶስ መፈተን

- ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ ተወሰደ። በዚያም ለአርባ ቀን በሰይጣን ተፈተነ። ኢየሱስ በእነኝህ አርባ ቀናት ፆመ። ማለትም ምንም ነገር አልበላም። ስለዚህም በጣም ተራበ።

- ሰይጣንም ይህ ኢየሱስን ለመፈተን መልካም አጋጣሚ እንደሆነ አየ። ኢየሱስን እነዲህ አለው "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነኝህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ አለው።" ኢየሱስም ከዘዳግም መፅሐፍ አንድ ቃል በመጥቀስ መለሰለት። "ሰው ከእግዚአብሔር በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" አለው።

- ከዚያም ሰይጣን ኢየሱስን ወደ አንድ ከፍተኛ ተራራ ወሰደውና የአለምን መንግስታት በሙሉ በአንድ ጊዜ አሳየው። እነኝህን መንግስታትም ለወደደው የመስጠት ስልጣን እንዳለው ነገረው።

- ሰይጣን ውሸታም እንደሆነ አትርሱ። እውነተኛ የምድር መንግስታት ገዢ እግዚአብሔር ነው፤ የመንግስትን ስልጣን ለሰዎች የሚሰጥ እርሱ ብቻ ነው። ሰይጣን ውሸታሙ ግን ኢየሱስ ለእርሱ ወድቆ ቢሰግድለት እነኝህን መንግስታት እንደሚሰጠው ይነግረዋል።

- "ሰይጣን ከእኔ ራቅ እንዲህ ተብሎ ተፅፏልና ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ።' ብሎ መለሰለት። አሁንም ኢየሱስ መልሶ የጠቀሰው ቃል የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በዘዳግም መፅሐፍ ውስጥ ነው።

- ሰይጣንም ለሶስተኛ ጊዜ ኢየሱስን ፈተነው። ኢየሱስን ወደ ኢየሩሳሌም አመጣውና በመቅደስ ጫፍ ላይ አቆመው። መላእክት እንደሚያገለግሉትና ጉዳት እንዳይደርስበት እንደሚጠነቀቁለት ካስታወሰው በኋላ ራሱን ከመቅደሱ ጫፍ ወደታች እንዲወረውር ይጠይቀዋል። በዚህን ጊዜ ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ቃል ጠቅሶ ነበር ኢየሱስን የፈተነው። የጠቀሰው ቃል የሚገኘውም በመዝሙር 91 ውስጥ የሚገኘውን ነው።

***"በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።"***

- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት " 'እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው።' ተብሎ ተፅፏል።"

- ሰይጣንም ተስፋ ቆርጦ ኢየሱስን ለጊዜው ትቶት ሄደ።

*የኢየሱስ ክርስቶስ መፈተን ታሪክ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 4፣ 1-13 ውስጥ ነው።*